መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
አቅራቢዎች

የሰው ሃዘን ጅማሬ



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሳሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus; Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): M. Maillot; Tammy S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2026 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ሁሉንም
ነገር ፈጠረ። እግዚአብሔር
የመጀመሪያው ሰው አዳምን
ሲፈጥር በኤደን ገነት
ውስጥ ከሚሰቱ ከሄዋን
ጋር ይኖር
ነበር።

እግዚአብሔርን በመታዘዙ
ፍጹም ደስተኛ ነበሩ አንድ
ቀን በህይወታቸው እስኪከሰት
ድረስ ከእግዚአብሔር
አብሯቸው ከመሆኑ
የተነሣ ነበር።

“ከየትኛውም
ዛፍ ፍሬ
እንዳትበሉ
እግዚአብሔር
ተናግሯችሁ ነበር?
በማለት እባቡም
ሔዋንን ጠየቃት።።”

ከሁሉም ዛፎች
ፍሬ እንድንበላ
ፍቅዶልናል
ነገር ግን አንዲት
ፍሬዋ የማይበላ ዛፍ
እንዳለች ነግሮኛል።
“እባቡም አትሞቱም”
ብሎ መለሠላት።

“እንደ
እግዚአብሔርም
ትሆናላችሁ”
አላቸው። ሔዋንም ከዚያ ዛፍ
ፍሬን ለመብላት አሠበች
እባቡንም ሠማች
እንዳላት ብዚያች
ዛፍ ፍሬን በላች።

ሔዋንም የእግዚአብሔርን
ትዕዛዝ ከተላለፈች በኋላ
ባሏም አዳም ከዚያች ዛፍ
ፍሬን እንዲበላ
ሰጠችው
እሱም
በላ።።

አዳምም ስትሰጠው “አይሆንም
የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ
ልንተላለፈው አይገባም”
ማለት ነበረበት።

አዳምና ሔዋን ታጢአትን
ከሠራ ወይም ካደረጉ በኋለ
እርቃናቸውን መሆናቸውን አወቁ።።

ለሀፍረታቸው
መሸፈኛ ይሆን ዘንድ ቅጠል
ሰፈተው ሀፍረታቸውን ሸፈኑት ከቁጥቋጠው
ሥር በመሸሸግም ከእግዚአብሔር ተደበቁ::

ፀሐይም ባዘቀዘቀች ጊዜ
እግዚአብሔርም ወደ
ኤደን ገነት ውስጥ መጣ።
አዳምና ሔዋን ያደረጉትን
ያውቅነበርና። አዳምም
በሔዋን ላይ አመካኘ
ሔዋንም በእባብ
አመካኘች።

እግዚአብሔርም እባብን
“የተረገምክሁን። ሴትቱም
በወላጀዋ ጊዜ በምጥ
ትውለድ” ብሎ ረገማቸው።

“አዳም አንተ ታጢአትን
ከመሥራትህ የተነሣ
ምድር ተረገመች እሾህንና
አሜክላን ታብቅል። ጥረህ
ግረህ የላብህን ወዝ
ፈሪዋንም ብላ”
አለው።

እግዚአብሔርም አዳምና
በሔዋንን ከኤደን ገነት
ውስጥ አሰወጣቸው
ምክንያቱም ...

... ኃጢአትን ሠርተዋልና
ህይወት ሰጪ ከሆነው
እግዚአብሔር
ተለይተዋል።።

እንደ እሳት
የሚንበለበሉ ሰይፎችንም
እግዚአብሔር በኤደን ገነት
ውስጥ አኖረ አስወጣቸውም
እግዚአብሔርም ለአዳምና
ለሔዋን የበግ
ለምድን አለበሳቸው።።

እግዚአብሔር ይህንን
እግዚአብሔርም ለአዳምና ለሔዋን
የበግ ለምድን አለበሳቸው።።
እግዚአብሔርም ይህንን
ለምድ ከየት
አመጣው?

በጊዜው አዳምና ሔዋን ልጆችን ወለዱ።
የመጀመሪያ ልጃቸውም ቃየል አትክልተኛ
ነበር። ሁለተኛው ልጃቸውም
አቤል ይባላል
እሱም
እረኛ
ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን ቃየል ለአምላኩ
ለእግዚአብሔር ከእርሻው ሰብል ሰጠታን
አመጣለት።።

አቤልም በጣም ምርጥ ከሚላቸው በጎች
መሃከል አንዱን መርጦ ለእግዚአብሔር
በስጦታ መልክ አመጣለት።
እግዚአብሔርም በአቤል
ስጦታ በጣም
ደስ ብሎት
ነበር።

እግዚአብሔር ቃየልና በመሥዋዕቱ ደስተኛ አልነበረም። ቃየልም በጣም ተናደደ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ አለ “ትክክለኛውን ነገር ካደረግክ ተቀባይነትን አታገኝምን?”

የቃየልም ጌዴት ከውሰጡ አልጣፋም ነበር።
ከእርሻው በኋላ ወንድሙን አቤልን
አደጋ አደረሰበት ከዚያም
በኋላ ገደለው።

እግዚአብሔርም ቃየልን እንዲህ አለው
“ወንድምህ አቤል ወዴት አለ?” “ከወዴት
እንዳለ አላውቅም” ብሎ
ዋሸው። “እኔ የወንድሜ
ጠባቂ ነኝን?”

አለው። እግዚአብሔርም አቤል
በመዋሸቱና እራሱን አዳኝ
በማስመሰል አራሽ (ገበሬ)
ሆኖ ሥጠታን በውሸት
በማቅረቡ ነው።

ቃየልም ከእግዚአብር ፊት ሸሸቶ
ሄደ። እሱም የአዳምንና የሔዋንን
ልጅ አገባ፡ ቤተሰባቸውንም
አሣደጉ።

በቅርቡም የቃል የልጅ ልጆችና፣
የልጅ ልጅ ልጆች ቃየልም
የመሠረታትን ከተማ ሞሉት።

የአዳምና የሔዋን ቤተሰብ በፍጥነት አደገ። በዚያን ዘመን የነበሩ ሠዎች ዛሬ ከሚኖሩት ሠዎች ይልቅ ረጅም ዕድሜ አላቸው።

ሴት ልጇ ሴት በተወለደችበት
ጊዜ ሔዋን እንደሀ አለች ...

... “በአቤል ምትክ እግዚአብሔርን
ሴትን ሰጥቶኛል ሴትም” ብዙ
ልጆችን ወለደ 912 ዓመት ኖረ።

በዚህ ዓለም ውስጥ በተለያዩ
ትውልዶች መሃከል ዓመጽ
እየበዛ መጣ፤ በመጨረሻም
እግዚአብሔር
የሠውን
ልጆች
ለማጥፋት
ወሠነ።

ሁሉም አውሬዎችና እንሰሳት።
እግዚአብሔር ሰው በመፍጠሩ
ተጸጸተ። ነገር ግን አንድ
ሰው እግዚአብሔርን
አስደሰተ።

ይህም ሰው ኖህ ይባላል። በሴት የዘር ሐረግ
የመጣ ነበር ኖህም ቅዱስና ነቀፌታ
የሌለበት ሰው ነበር አካሄዱንም
ከክእግዚአብሔር
ጋር ያደረግ ነበር።

ሦስቱ ልጆቹም እግዚአብሄርን እንደታዘዙ
አስተማራቸው። እንግዳና አዲስ
በሆነ መንገድ እግዚአብሔር
ኖህን ለራሱ ለመጠቀም
መረጠው።

የሰው ሃዘን ጅማሬ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ 3-6

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን
ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን
በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር
እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው
ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና
ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት
እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ
በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሰማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን
እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር
እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል።
እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ
ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ
ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ
አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል
ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ሀያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ
ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን
ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር
ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ
ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ
ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16